**Español:** masspowerchoice.com/cambridge/spanish
**Kreyòl ayisyen:** masspowerchoice.com/cambridge/hcreole
বাংলা**:** masspowerchoice.com/cambridge/bengali
አማርኛ**:** masspowerchoice.com/cambridge/amharic
masspowerchoice.com/cambridge/arabic **عربى**

# የካምብሪጅ ከተማ

## በኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋ ላይ የክፍያ ለውጥ ስለመደረጉ ከከተማው የተሰጠ ማስታወቅያ

ታህሳስ (December) 12 ቀን 2023

ውድ የካምብሪጅ ኤሌክትሪክ ደንበኛ፤

**ይህ ማስታወቅያ፤ በኤቨርሶርስ (Eversource) የኤሌክትሪክ ክፍያ ላይ ስለተደረገው ለውጥ አስፈላጊ መረጃ የያዘ ነው።**

የእርሶ የኤሌክትሪክ ሂሳብ፤ የከተማይቱ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም በሆነው በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) ውስጥ የተጠቃለለ ነው። ይህ ፕሮግራም በኤቨርሶርስ (Eversource) የሚያገኙት የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋ፤ በካምብሪጅ ዋጋ እንዲታሰብሎት የሚያደርግ ነው። እርሶ አሁን የገቡበት አማራጭ **100% ግሪን ፕላስ** (100% Green Plus) የተባለው አማራጭ ነው፤ ይህም ማለት የሚያገኙት ኤሌክትሪክ መቶ በመቶ በከተማይቱ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም ውስጥ ከሚገኘው ከኤም ኤ ክፍል አንድ (MA Class I) የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ፕሮጀክት ነው ማለት ነው።

በቀጥታ ከዳይሬክት ኤነርጂ አገልግሎት (Direct Energy Services, LLC, ("Direct Energy") ጋር ትስስር ያለው የካምብሪጅ ወቅታዊ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ኮንትራት/ውል በጥር (January) ወር ያከትማል። በምትኩም አዲስ የ24-ወራት ኮንትራክት/ውል ስራውን ይጀምራል። **አዲሱ ውል አዲስ ዋጋዎችን ያስከትላል።**

የወቅቱ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ውል በ2020 ነበር የተፈረመው። ይህም የምንከፍለውን ክፍያ በጣም ዝቅ አድርጎት ቆይቷል። ። ይሁንና ከዛን ግዜ ጀምሮ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋ፤ በዓለም ገበያ ውስጥ የሃይል/ኤነርጂ ሁኔታ ስለሚለውወጥ፤ ከፍ እያለ ሲመጣ ቆይቷል። ይሄው የካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ አቅርቦት (Cambridge Community Electricity Program )ዋጋም፤ የዳይሬክት ኤነርጂ (Direct Energy) ውል በተግባር መተርጎም ሲጀምር፤ ከዓለም ገብያ ጋር የሚመጣጠን ይሆናል።

- **በ100% ግሪን ፕላስ አማራጭ (100% Green Plus option) አዲስ ዋጋ፡ ለአንድ ኪሎዋት (¢/kWh) 16.82 ሳንቲም ነው።**
  ይህ አዲስ ዋጋ ከጥር (January) 2024 እስከ ጥር (January) 2026 ለ24 ወራት የሚዘልቅ ነው።

  ይህ አዲስ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋ  አሁን ከምትከፍሉት ዋጋ ከፍ ያለ ነው ግን ኤቨርሶርስ( Eversource) በመጪው ግዜያት፤ ከጥር (January) 1ቀን እስከ ሓምሌ (July) 31 ቀን 2024 ድረስ ተግባራዊ ከሚያደርገው ለአንድ ኪሎዋት (¢/kWh) የ17.251 ሳንቲም የመኖርያ ቤቶች የአገልግሎት ዋጋ፤ ዝቅ ያለ ነው። *የኤቨርሶርስ (Eversource) ዋጋ በየግዜው ስለሚቀያየርና  የመጪ ግዜያት ዋጋ ስለማይታወቅ፤ ከዚህ ቀን በኋላ የገንዘብ ቁጠባ ያደርጋሉ ብለን ዋስትና ለመስጠት እንደማይቻል እባኮን ይገንዘቡ።*

## ያሉት አማራጮች:

- **ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወስዱ በዛው ባሉበት የካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) ውስጥ መቆየት።** በዚህ የ100% ግሪን ፕላስ (100% Green Plus) አማራጭ ለመቆየት ከፈለጉ፤ ምንም ዓይነት እርምጃ መውሰድ አያስፈልጎትም። በፕሮግራሙ የመቀጠል ሁኔታዎ (ምዝገባዎ)፤ በ ጥር ወር (January) 2024 የሚጀምረው ዋጋ ይዞ ራሱ በኦቶማቲክ መንገድ ይታደሳል። በአዲሱ ዋጋ የተተመነውን የኤቨርሶርስ (Eversource) የኤሌክትሪክ ሂሳቦን በየካቲት ወር (February) 2024 ያዩታል።

- **በፕሮግራሙ ውስጥ ወዳለው ወደ ሌላ አማራጭ መግባት፤** የኤሌክትሪክ ዋጋዎ 50%  እንዲጎድልዎት ከፈለጉ ስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) የተሰኘውን አማራጭ በመምረጥ፤ ከ ኤም ኤ ክፍል 1(MA Class I) የሚታደስ ኤነርጂ ማግኘት ይችላሉ። ወይም የኤኮኖሚ ግሪን (Economy Green ) የተሰኘውን አማራጭ በመውሰድ ህጉ የሚፈቅደውን አነስተኛ ዋጋ መምረጥ ይችላሉ።

- **ካለ ምንም የመውጭያ ክፍያ ወይም መቀጮ ፕሮግራሙን ለቀው መውጣት ይችላሉ።** ወደ ኤቨርሶርስ መሰረታዊ አገልግሎት (Eversource's Basic Service) ለመመለስ ከፈለጉ ወይም ከሌላ የኤሌክትሪክ አቅራቢ ጋር የራስዎን ውል መፈራረም ከፈለጉም ነጻነቱ አሎት።

ለውጥ ለማድረግ፤ MassPowerChoice.com/Cambridge ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 1-844-379-9934 ደውለው በከተማው ፕሮግራም ውስጥ ካሉት አማካሪዎች ጋር ተመካከሩ። ስልክ ሲደውሉ የኤቨርሶርስ (Eversource) የኤሌክትሪክ ሂሳብ ቁጥሮን ይያዙ።

(በስተጀርባ ተጨማሪ መረጃ ይገኛሉ። ▶)

# በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) ያሉን አማራጮች

ከታች ያለው ሰንጠረዥ፣ ባለው ወቅታዊ አማራጭ መቆየት ወይም ሌላ አማራጭ መውሰድ ወይም ሙሉ በሙሉ ከፕሮግራሙ ወጥተው ወደ ኤቨርሶርስ መሰረታዊ አገልግሎት (Eversource's Basic Service) መመለስ ከሚሉት አማራጮች አንዱን መምረጥ እንዲችሉ ያግዞታል። ለውጥ ለማድረግ MassPowerChoice.com/Cambridge ይጎብኙ ወይም በከተማው ውስጥ ካሉት የፕሮግራሙ አማካሪዎች ጋር በስልክ ቁጥር1-844-379-9934 በመደወል ተነጋገሩ።

**በካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም (Cambridge Community Electricity Program) ያሉት አማራጮች**

**እርሶ የተመዘገቡት እዚህኛው ላይ ነው። ▼**

**ለመሳተፍ ካልፈለጉ፤**

| | | ኤኮኖሚ ግሪን (Economy Green) በህግ የሚፈቀድ አነስተኛው የሚታደስ ኤነርጂ/ ሃይል | ስታንዳርድ ፍሪን (Standard Green) ከኤም ኤ ክላስ 1 (MA Class 1) 50% የሚታደስ የሃይል ፕሮጀክት | 100% ግሪን ፕላስ (100% Green Plus) ከኤም ኤ ክላስ 1 (MA Class 1) 100% የሚታደስ የሃይል ፕሮጀክት | የኤቨርሶርስ መሰረታዊ አገልግሎት (Eversource's Basic Service) ከወጡ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ዋጋ** | | 13.82 ¢/kWh (ኪሎዋት)* | 14.81 ¢/kWh (ኪሎዋት)* | 16.82 ¢/kWh (ኪሎዋት)* | 17.251 ¢/kWh - መኖርያ ቤቶች<br>17.587 ¢/kWh - ትናንሽ ንግድ ቤቶች<br>19.098 ¢/kWh - ትላልቅ ንግድ ቤቶች |
| **ዋጋው የሚቆይበት ግዜ** | | ጥር (January) 2024 እስከ ጥር (January) 2026 | ጥር (January) 2024 እስከ ጥር (January) 2026 | ጥር (January) 2024 እስከ ጥር (January) 2026 | ከጥር (January) 1 ቀን እስከ ሓምሌ (July) 31 ቀን 2024 መኖርያ ቤቶችና ትናንሽ ንግድ ቤቶች ከጥር (January) 1 ቀን እስከ ሚያዝያ (April) 30 ቀን 2024 ትላልቅ ንግድ ቤቶች |
| **ከኤም ኤ ክፍል 1 (MA Class 1) የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይል ፕሮጀክት የሚገኝ ኤሌክትሪክ** | | | | | |
| በካምብሪጅ የተጨመረ | 2024 | - | 26% | 76% | - |
| | 2025 | - | 23% | 73% | - |
| | 2026 | - | 20% | 70% | - |
| በክፍለሃገሩ ህግ የሚጠየቅ | 2024 | 24% | 24% | 24% | 24% |
| | 2025 | 27% | 27% | 27% | 27% |
| | 2026 | 30% | 30% | 30% | 30% |
| ድምር | **2024** | **24%** | **50%** | **100%** | **24%** |
| | **2025** | **27%** | **50%** | **100%** | **27%** |
| | **2026** | **30%** | **50%** | **100%** | **30%** |
| **ከሌሎች ንጹህ ወይም የሚታደስ ምንጮች የሚገኝ ኤሌክትሪክ **** | | | | | |
| በክፍለሃገሩ ህግ የሚጠየቅ | 2024 | 38% | 38% | 38% | 38% |
| | 2025 | 36% | 36% | 36% | 36% |
| | 2026 | 39% | 39% | 39% | 39% |
| **የመውጫያ ውሎች** | | ባፈለጉት ግዜ ይውጡ የመውጫያ ክፍያ/ መቀጮ የለም። | ባፈለጉት ግዜ ይውጡ የመውጫያ ክፍያ/ መቀጮ የለም። | ባፈለጉት ግዜ ይውጡ የመውጫያ ክፍያ/ መቀጮ የለም። | መውጣት ከፈለጉ በማንኛውም ግዜ መውጣት ይችላሉ። የሚከፈል የመውጣት ክፍያ ወይም መቀጮ የለም። |

* ዋጋዎች ለአንድ ኪሎዋት የ$0.00075/kWh የአስተዳደር ክፍያን ያጠቃልላሉ። በተጨማሪም በካምብሪጅ ውስጥ የሚታደስ የኤሌክትሪክ ሃይልን ለማጠናከር የሚደግፍ በኪሎዋት የ $0.002/kWh የስራ ማካሄጃ ክፍያን ያጠቃልላሉ። ቀጥታዊ የሆነ የቁሳቁስ ዋጋ ጭማሪ ካገጠመ ግን ያ በውል የተደረሰው የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋ ሊጨምር ይችላል።

** የማሳሹሴትስ ኮመንዌልት (Commonwealth of Massachusetts) አስተዳደር፤ በ2024 የኤሌክትሪክ አቅርቦት ቁሳቁሶች በሙሉ ቢያንስ 62%ው፣ በ2025 ደግሞ 63%ው እንዲሁም በ2026 69% ከንጹህ ወይም ከሚታደስ የሃይል ምንጮች እንዲሆን ይጠይቃል። ዳይሬክት ኤነርጂ (Direct Energy)ሁሉንም የኤሌክትሪክ ሃይሉን ከኤም ኤ ክላስ 1 (MA Class 1) የሚታደስ የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክትና ከሌሎች እንደ የሃይልና የኑክሊየር ምንጮች ከመሳሰሉት መገብየት አለበት። ለዚህም ኤኮኖሚ ግሪን (Economy Green) የተባለው ዝቅተኛውን ብቁነት ያሟላል። ስታንዳርድ ግሪን (Standard Green) እና 100% ግሪን ፕላስ (100% Green Plus) የተባሉት አማራጮች ከ ከኤም ኤ ክላስ 1 (MA Class 1) ተጨማሪ ኤሌክትሪክ በመግዛታቸው ይበልጡታል።

**ስለ ካምብሪጅ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም የበለጠ መረጃ ለማግኘት ወይም ለጥያቄያችሁ መልስ ለማግኘት፤ የካምብሪጅ ከተማ በ2024 መጀመርያ ላይ ሁለት ስብሰባዎችን ወይም ዌብናርሶችን (webinars) ያሰተናግዳል።**

**▶ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ወይም ለመመዝገብ፡ www.MassPowerChoice.com/Cambridge ይጎብኙ።**